የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ ሰኔ 9 ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 28
ADDIS ABABA 16th June, 2006

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፪/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ለአፋር ክልል ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከኩዌት ፈንድ ለአረብ የኢኮኖሚ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፬፻፲፰

## CONTENTS

Proclamation No. 492/2006

Kuwait Fund For Arab Economic Development Loan Agreement for financing Extension of the National Power Grid to the Afar Region Project Ratification Proclamation…. Page 3418

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፪/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ የኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አ ዋ ጅ

ለአፋር ክልል የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፲፩ሚሊዮን የኩዌት ዲናር /አሥራ አንድ ሚሊዮን የኩዌት ዲናር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ የኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ፌብሩዋሪ ፰ ቀን ፪ሺ፮ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአፋር ክልል የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከኩዌት ፈንድ ለአረብ የኢኮኖሚ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፪/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION NO. 492/2006.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE KUWAIT FUND FOR ARAB ECONOMIC DEVELOPMENT

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund For Arab Economic Development stipulating that the Kuwait Fund for Arab Economic development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in an amount not exceeding KD 11,000,000 (eleven million Kuwait Dinar) for financing Extension of the National Power Grid to the Afar Region Project, was signed in Addis Ababa on the 8th day of February 2006;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 1st day of June, 2006;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:-

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Kuwait Fund For Arab Economic Development Loan Agreement for Financing Extension of the National Power Grid to the Afar Region Project Ratification Proclamation No.492/2006."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ የኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ፌብሩዋሪ ፰ ቀን ፪ሺ፮ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው ቁጥር 717 የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፩ሚሊዮን የኩዌት ዲናር /አሥራ አንድ ሚሊዮን የኩዌት ዲናር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 9 ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement No. 717 signed in Addis Ababa on the 8th day of February 2006 between the Federal democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development is ratified;

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of KD 11,000,000 (eleven million Kuwait Dinar) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of June, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት